# እባካችሁ እዘኑለት!

«መጀመሪያ ቃል ነበረ. . .
ቃልም ጸንቶ ሥጋ ሆነ . . .»

ከዘፍጥረት ሕይወት ዓለም፣ - ከአእምሮ ሕያው ቅመም፣
የፈለቀ የባህል ሃብት፣- የዳበረ በሊቃውንት፣
በሰው ልጆች የሰረጸ፣- ሆሄ ፊደል . . . ያስቀረጸ፣

ቋንቋ 'ኮ ነው የመግባቢያ፣ - የአህዛብ መወያያ::

እባካችሁ እዘኑለት! - ቃል ክቡር ነው የእግዜር ፍጥረት!

የሕዝብን ቅርስ ምርጥ ቃላት፣ - ያላግባቡ ትርጉም መንሳት፣
እንደ ብስና ክፉ ግሳት፣ - እንዳመጣ ቃላት መትፋት፣
ያስነውራል! ያሳፍራል! - ቀፎ አንጎል ያስገምታል!

«እንከን-የለሽ»፣ «ተዓማኒ»፣ «ሰላማዊ»፣ «ነጻ ምርጫ»...፣
«ፍትሃዊ»፣ «ዴሞክራሲ»... «የሕዝብ ድምጽ»፣ «አብላጫ»፤
ትርጉማችሁ . . . ትርጉማችን፣
ላይጣጣም  የቃላችን፣
እያወራን አንድ ቋንቋ፣
እንዴት እኮ ልንግባባ?!
እባካችሁ ስለ እግዚአብሔር፣ ውብ ቃላትን አታርክሱ፣
በናንተ አፍ አይነገር፤ በማታፍሩ... በማትሳሱ፤
ኧረ! አይቆሽሽ «ዴሞክራሲ». . .ያ! ብርቱ ቃል የአቴና . . .፣
የአርስቶትል፣ የሶቅራጠስ፣ የሆሜር. . . ቅርስ ገናና!
ለአፋችሁ ለከት ይበጅ፣
አታርክሱ  ቃላት ባዋጅ!

ድጓ ቅኔ ያስጠረዘ፣ - መቃብዕር ያስቀረጸ፣
ስንት ጠቢብ ያፈራ፣ - ያገር አድባር ያኮራ፣
የጥንት አበው ሊቃውንቱ፣ - የትውልድ ሰንሰለቱ፣
. . .የዮፍታሔ...፣ የሐዲስ...፣ የጸጋዬ...፣ የበዓሉ. . .፣
ቃል ኦኮ ነው ድንቅ ውሉ!

ባለ ጊዜ፣ ባለ ሃብት፣ ባለ አገር፣ ባለ ምርጫ..
ባለ ስልጣን፣ ባለ ብረት፣ ባለጉልበት፣ ባለ ጡጫ፤
አገር-አልባ፣ ፍትህ-አልባ፣ ርትዕ-አልባ.. ስታደርጉን፣
ቃልን እንኳ ብትተውልን፣ ልሳን-አልባ ባታደርጉን፤
እባካችሁ እዘኑለት፤
ለሥነ-ቃል ኃያል ውበት፤
እንደ አክታ ጸያፍ ትፋት፣
ያለቦታው አትለጥፉት!

ጌታቸው አበራ
ግንቦት 2002 ዓ/ም
(ሜይ 2010)